Arlington Public Schools

# 2022 የትምህርት ቤት









**በሕዳር 8 የምርጫ ቀን፣ የአርሊንግተን መራጮች ነባሩን የትምህርት ቤት የመሰረተ ልማት ለማሻሻልና ለማጎልበት $165.01 ሚሊዮን ዶላር የትምህርት ቤት ቦንዶችን እንዲያጸድቁ ይጠየቃሉ። በተጨማሪም የትምህርት ቤቱ ቦንድ የሙሉ ጊዜ የአርሊንግተን የስራ ማእከል ተማሪዎችን፣ ሁሉንም የAPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ለማገልገልና ለወደፊት የተሳትፎ እድገት ለመዘጋጀት አዲሱን መገልገያ በገንዘብ ይደግፋል። የትምህርት ቤቱ ቦንድ የ APS ትምህርት ቤት መገልገያዎች የተማሪዎችን ተለዋዋጭ የሆኑ ፍላጎቶች እንዲሟሉ ለማስቻል፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እድዲሰጥ ድጋፍ ለማድረግና በ APS መገልገያዎች ላይ መዋእለ ንዋይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱም ለማህረሰቡ የሚጠቅሙ የተለያዩ አላማዎች ላይ የሚውሉ በመሆኑ እንደ ማህበረሰብ ንብረቶች የሁለትዮሽ ሚና ኖሯቸው ስለሚያገለግሉ ነው።**

### ከ2022 የትምህርት ቤት ቦንድ ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ድጋፍ በአርሊንግተን ያሉ ትምህርት ቤቶችን ፍላጎቶችን በማሟላት ረገድ እንዴት ያግዛል?

የ2022 የትምህርት ቤት ቦንድ ገንዘብ የትምህርት ክፍሉን ነባር የመሰረተ ልማት ለማሻሻልና ለማጎልበት እንዲሁም በአርሊንግተን የሙያ ማእከል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው አዲስ መገልገያ ለመገንባት ለአመታዊና ተከታታይ ኢንቨስትመንት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ ነው። የትምህርት ቤቱ ቦንድ የ APS ለቀጣይ ማሻሻያዎችና አሁን ላይ ያለውን የ APS መገልገያ ማሻሻያዎች በቀጣይነት ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። የተማሪዎችን ጤናና ደህንነት ለማሳደግ የሚረዱ ፕሮጀክቶች አብዛኛውን የተዘረዘሩ ስራዎችን ጨምረው የያዙ ናቸው። የተሻሻሉ ማብሰያ ቤቶች ተማሪዎች በቦታው ላይ የሚዘጋጁ ተጨማሪ ትኩስ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን ያካተቱ ጥራታቸውን የጠበቁ ምግቦችን እንዲመገቡ የሚያስችላቸው ነው። ሁሉም ጎብኚዎች በዋናው መስሪያ ቤት መግባታቸውን በሚያረጋግጡበት ወቅት የመግቢያና የደህንነት መተላለፊያ ማሻሻያ ወቅታዊውን የደህንነት ደረጃዎችን የሚከተል ነው።

### የትምህርት ቤት ቦንድ የሚሰራው እንዴት ነው?

ልክ ከግለሰብ ወይም ቤተሰብ እንደተገኘ የቤት መስሪያ ብድር ሁሉ ቦንዶችም የረጅም ጊዜ ብድሮች ሆነው ወጪው ለዋና ዋና የካፒታል ማሻሻያዎች ለአመታት ተከፋፍሎ የሚመደብ ነው። ረጅም ጊዜ ለሚወስዱ ኢንቨስትመንቶች (ለምሳሌ የትምህርት ቤት ግንባታ) በቦንድ ክፍያን መፈጸም ወጭውን በትምህርት ቤቶች ውስጥ እየተካሄደ ባለው ኢንቨስትመንት ተጠቃሚ በሚሆኑ የአሁንና የወደፊት ግብር ከፋዮች መካከል ያለውን ወጪ እንዲሰራጭ የሚያደርግ ነው።

### የ 2022 የትምህርት ቤት ቦንድን መጠቀም የሚቻለው እንዴት ነው?

$165.01 ሚሊዮን ዶላር ለሚከተሉት ፕሮጀክቶች ይውላል፡

- ዋና ዋና የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች HVAC፣ ኤሌክትሪክ፣ መብራት፣ ጣሪያና መስኮትን ጨምሮ - የገንዘብ ድጋፍ፡ $16.8 ሚሊዮን ዶላር
- የመግቢያ/የደህንነት መግቢያ ማሻሻያና የማብሰያ ቤት እድሳት አሁን ያለውን የደህንነት መስፈርቶች ለማሟላት እንዲሁም ለተማሪዎች በቦታው የተዘጋጁ ጤናማ ምግቦችን ለማቅረብ። - የገንዘብ ድጋፍ፡ $16.36 ሚሊዮን ዶላር (በ 2021 የትምህርት ቤት ቦንድ ህዝበ ውሳኔ $4.12 ሚሊዮን ተካቷል)
- የአርሊንግተን የሙያ ማእከል ፕሮጀክት የተማሪዎችን የሙሉ ጊዜ የአርሊንግተን የሙያ ማእከል (ACC) ተማሪዎችና ከሁሉም የ APS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙያና ቴክኒካል ትምህርት (CTE) ትምህርቶች በ ACC የተመዘገቡ ተማሪዎችን ለመደገፍ የሚያስችል ዘመናዊ መገልገያ ለመገንባት - የገንዘብ ድጋፍ፡ $135.97 ሚሊዮን ዶላር

### የትምርት ቤቱ ቦንድ ከ CIP ጋር እንዴት ይዛመዳል?

የ 2022 የትምህርት ቤት ቦንድ ህዝበ ውሳኔ የሚደረገው ለ $165.01 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ለአዲሱን የአርሊንግተን የሙያ ማእከልን ጨምሮ በ 2023-32 የካፒታል ማሻሻያ እቅድ (CIP) ለተለያዩ የ APS ካፒታል ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። የ 2022 የትምህርት ቤት ቦንድ በ 2023-32 CIP አንዳንድ ፕሮጀክቶችን የሚሸፍን ሲሆን ይህም የወደፊት የትምህርት ቤት ቦንዶችን ጨምሮ በ 2023-32 CIP በዋነኝነት የሚያተኩረው በ 10-አመት ጊዜ ውስጥ ባሉ የ APS መገልገያዎች ላይ ባሉ ፕሮጀክቶችና በተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ላይ ነው።




FY 2023-32 CIP ገንዘቡን እንደሚከተለው መድቧል፡

- የረጅም ጊዜ እድሳት እቅድ የወደፊት የገንዘብ ድጋፍን ሳያካትት 55% ለነባር መገልገያዎች ማሻሻያ
- ለ ACC ፕሮጀክት 45% (አዲስ ህንጻ፣ ሜዳ፣ የመኪና ማቆሚያ ጋራጅ)

# 2022 የትምህርት ቤት

### ቀደም ብለው በነበሩ ቦንዶች የተጠናቀቁት የ APS ፕሮጀክቶች የትኞቹ ናቸው?

በአርሊንግተን ማህበረሰብ ከዚህ ቀደም የጸደቁ ቦንዶች ለነባር የትምህርት ቤት ህንጻዎች እድሳትና የማስፋፊያ ስራዎች እንዲሁም ለአዳዲስ ግንባታዎች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ የቅርብ ጊዜ ፕሮጀክቶችን ከመደገፍ አንጻር ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል፡

- የቀድሞው የ APS የትምህርት ማእከል (ነሐሴ 2022 የተከፈተ) በዋሽንግተን-ሊብሪቲ ቅጥያ ተጨማሪ 600 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መቀመጫዎች
- የካርዲናል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ (ነሐሴ 2021 የተከፈተ)
- የትራንስፖርት ሰራተኞች መገልገያ እድሳት (መጋቢት 2021 የተከፈተ)
- የዶርቲ ሃም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጭማሪና እድሳት (እድሳት መስከረም 2019 ተከፍቷል፣ ጭማሪው በመስከረም 2020 ተከፍቷል)
- የ H-B ዉድላውንና ሺቨር ፕሮግራሞችን የከፍታ ግንባታ (መስከረም 2019 የተከፈተ)
- የአሊስ W. ፍሊት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ (መስከረም 2019 የተከፈተ)
- ለአቢንግዶን አንደኛ ደረጃ ጭማሪና እድሳት (ጥር 2018 የተከፈተ)
- የሚክንሊ አንደኛ ደረጃ እድሳትና ማስፋፊያዎች (በ 2016 በልግ ተጠናቋል)
- ዲስከቨሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ (በ 2015 በልግ የተከፈተ)

### በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተነሳ የAPS ካፒታል ማሻሻያ እቅድ ሂደት እንዴት ተጎዳ?

የ FY 2023-32 CIP በአርት አመታት ውስጥ የመጀመሪያው CIP ሲሆን በዋናነት ለተማሪ ተሳትፎ በዋነኛነት ምላሽ የማይሰጥና በ APS የተማሪ ስኬትና ደህንነት ላይ የሚያተኩር ነው። ተማሪዎች ትምህርታቸውን የሚደግፉ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የማስተማሪያ አካባቢዎችን ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት የትምህርት ቤቱን ነባር መሰረተ ልማት ለማሻሻልና በአርሊንግተን የሙያ ማእከል ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው አዲስ መገልገያ ለመገንባት እቅድ በማውጣት የ 2023-32 CIP በተለይ ለአመታዊና ተከታታይ ኢንቨስትመንት ቅድሚያ ይሰጣል። የ FY 2023-32 CIP ዝርዝር፣ APS ቀጣይ ማሻሻያዎችንና የአሁን የ APS መገልገያ ማሻሻያዎችን በሂደት ላይ እያለ ቅድሚያ በሚሰጠው አኳሃን እንዴት እንደሚያቅድ ይገልጻል። የተማሪዎችን ጤናና ደህንነት ለማሳደግ የሚረዱ ፕሮጀክቶች አብዛኛውን የተዘረዘሩ ስራዎችን አካተው የያዙ ናቸው።

### እያደገ የመጣውን ተሳትፎና የትምህርት ቤት አቅም ፍላጎቶችን ለመፍታት APS ከአርሊንግተን ካውንቲ መንግስት ጋር እንዴት እየሰራ ነው?

APS የሶስት-A (AAA) ቦንድ ደረጃ ካለው ከአርሊንግተን ካውንቲ ጋር በቅርበት ተባብሮ ለመስራት ቁርጠኛነቱ ያለው ሲሆን የአርሊንግተንን የትምህርት ቤት መገልገያዎች የተማሪን ትምህርት በብቃት ባለው መንገድ ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው። APS በአርሊንግተን ካውንቲ የወጡትን ሁሉንም ከእዳ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፖሊሲዎች ይከተላል። ከአማካሪ ኮሚቴዎች ጋር APS በቅርበት የሚሰራ ሲሆን የአርሊንግተን ካውንቲ የወደፊት የካፒታል ማሻሻያ ፍላጎቶችን ለመገምገምና ለመፍታት አጠቃላይ አቀራረብን ይፈጥራል።

### በAPS የሚማሩ ልጆች ለሌላቸው የአርሊንግተን ነዋሪዎች የትምህርት ቤት ቦንዶች እንዴት ሊጠቅማቸው ይችላል?

ሁሉም ነዋሪዎች በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ቤታችን እየተማሩ ያሉ ልጆች ባይኖራቸውም አሁን ላይ ተማሪዎች የሌላቸው የ APS ተመራቂዎች ያሏቸው ቤተሰቦች እንዲሁም የወደፊት ተማሪዎችን በ APS ለማስተማር ያቀዱ ቤተሰቦችን የሚጨምር ነው። የትምህርት ቤት ስርአታችንን ጠንካራነት የሚያስጠብቁ ኢንቨስትመንቶች በአርሊንግተን ለሚኖሩ ሁሉ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ጥቅም አላቸው፡

1. የ APS መገልገያዎች የማህበረሰብ አጠቃቀም - የ APS መገልገያዎች በመላው የአርሊንግተን ማህበረሰብ ከ 58,000 ሰአታት በላይ ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ እነዚህም የሚያጠቃልሉት፡ በውሃ አካላት መገልገያዎች ላይ የማህበረሰብ አባልነት፣ በአርሊንግተን ካውንቲ ፓርኮችና መዝናኛ የሚካሄዱ የምሽት እንዲሁም የሳምንት መጨረሻ ፕሮግራሞች፣ ትምህርት ቤቶች በሚዘጉበት ጊዜ የበአልና የበጋ ካምፖች እንዲሁም ሰፊ የማህበረሰብ ማንቂያ ዝግጅቶች፣ የስነ ጥበብ ዝግጅቶችና ሌሎች ልዩ ስብሰባዎች።
2. በኢኮኖሚ ላይ የሚኖር ተጽእኖ - ምንም ይሁን ምን ነዋሪው በአሁኑ ጊዜ በ APS የሚማሩ ልጆች ቢኖራቸውም፣ ለትምህርት ቤት ስራዎችና ለካፒታል ማሻሻያዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ በአርሊንግተን ካውንቲ የወደፊት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል። ኢኮኖሚስት በሆኑት ዶ/ር ማይክል ዋልደን በ 2013 የተደረገው ጥናት እንዳመላከቱ ለ APS ካፒታል ማሻሻያ እቅዶች የሚወጣው እያንዳንዱ $1 ሚሊዮን ዶላር 10.4 አርሊንግተን ስራዎችን ከመፍጠር ጋር ተያያዥነት አለው። በተጨማሪነትም መሻሻል የታየበት የ APS የተማሪ አፈጻጸም የንብረት ዋጋና ገቢ እንዲጨምር አድርጓል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ልክ እንደ Nestlé እና Amazon ያሉ ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች በአርሊንግተን ውስጥ ቢሮዎችን ለማግኘት በተደረገው ውሳኔ የትምህርት ስርአቱ ጥራት ዋነኛ ምክንያት መሆኑን አሳይተዋል።

### ተጨማሪ መረጃን የት ማግኘት እችላለሁ?

በ 2022 የትምህርት ቤት ቦንድና በ FY 2023-32 የ APS ካፒታል ማሻሻያ እቅድ (CIP) የታቀዱ ሁሉም

ፕሮጀክቶች ላይ መረጃ በመስመር www.apsva.us/CIP ላይ ይገኛል።

የትምህርት ቤቱ ቦንድ በሕዳር 2/2021 የምርጫ መስጫ የሚካሄድ ይሆናል። ድምጽ ለመስጠት ሶስት መንገዶች አሉ፡

- ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት፡ ከመስከረም 23/2022 ጀምሮ በአርሊንግተን ውስጥ ካሉ አምስት ቦታዎች ይምረጡ
- በደብዳቤ፡ ጥቅምት 28/2022 ድምጽ በደብዳቤ መስጠት
- በአካል በመገኘት፡ በምርጫ ቦታዎ - በህዳር 8/2022 ከ 6 ኤ.ኤም - 7 ፒ.ኤም ይከፈታል

**ቦታውን ለማግኘት ወይም ድምጽ በደብዳቤ ለመስተት ለመጠየቅ ይህን ይጎብኙ፡ vote.arlingtonva.us**